# የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን

# የማስረጃ አቀራረብ ስርዓት አፈፃፀም

# መመሪያ ቁጥር 3/2012

# መግቢያ

ባለስልጣን መ/ቤቱ በፍትህ አካላት ፊት የሚያቀርባቸውን ክሶችና አቤቱታዎች በማስረጃ አስደግፎ ሙግት ማካሄድ ለውጤት ማብቃቱ የሚታወቅ በመሆኑ ፣

የሚቀርቡት ክሶች በማስረጃ ጉድለት ምክንያት በሚሰጥ ፍርድ ባለስልጣን መ/ቤቱ መብትና ጥቅሙን እንዳያጣ እና የባለስልጣኑን በፍትህ አካላት ዘንድ የሚቀርብበትን ማንኛውም አይነት ክሶችና አቤቱታዎች በአግባቡ እንዲከላከል እንዲሁም የባለስልጣኑን መብትና ጥቅም በአግባቡ እንዲጠብቅ መደረግ ያለበት መሆኑ በመታመኑ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 35/2004 አንቀጽ 53 ንዑስ አንቀጽ 2 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### አንቀፅ አንድ

### አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ ‹‹የማስረጃ አቀራረብ ስርአት መመሪያ ቁጥር 3/2012›› ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### አንቀፅ ሁለት

### ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ ያሉ ቃላትና ሀረጎች የሚከተለውን ትርጉም ይይዛሉ ፡-

1. “**ባለስልጣኑ**”ማለት፡- የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን መስሪያ ቤት ነው፡
2. **“ጽ/ቤት”** ማለት የባለስልጣኑ የውሃና ሳኒቴሽን ልማትና ማስፋፊያ ኘሮጀክት ጽ/ቤት ነው፡፡
3. **“ሥራ ክፍሎች”**፡- ማለት የባለስልጣኑና የጽ/ቤቱ ዘርፎች እና በዘርፎቹ ሥር የሚገኙ ደጋፊ፣ አብይ እና ንዑስ የሥራ ሂደቶች ነው፡፡
4. **“ደጋፊ የሥራ ሂደት”፡-** ማለት የሕግና ኢንሹራንስ ደ/የሥራ/ሂደት ነው፡፡

5. **"የፍትህ አካል"** ማለት፡- የፖሊስ ጽ/ቤት፣ የአቃቢ ህግ መ/ቤት፣ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ እና በተለያየ ደረጃ የተቋቋሙ የፌዴራል፣ የክልልና የከተማ ፍርድ ቤቶች ነው፡፡
6. **"ማስረጃ"** ማለት፡- ክስን ወይም መልስን ለማጠናከር ወይም ለማስተባበል የሚጠቅም ሰነድ ወይም የሰው ምስክር ነው፡፡
7. **"ክስ"** ማለት፡- መ/ቤቱ ጥቅሙን ለማስጠበቅ ለፍትህ አካላት የሚያቀርበው የጽሁፍ አቤቱታ ነው፡፡
8. **"መልስ"** ማለት፡- መ/ቤቱ ላይ ለቀረበበት ክስ ለፍትህ አካላት የሚሰጥ በጽሁፍ የሚቀርብ መከላከያ ነው፡፡

## <u>አንቀፅ ሶስት</u>

## <u>የመመሪያው የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ ደጋፊ የስራ ሂደቱ ክስ ወይም መልስ ለማቅረብ እንዲሁም የህግ አሰተያየት ለመስጠትና የየኢንሹራንስ ስርዓቶችን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉትን ማስረጃዎች ከሥራ ክፍሎች የሚላኩበት ሥርዓት ላይ ብቻ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

## <u>አንቀፅ አራት</u>

## <u>የጾታ አገላለፅ</u>

በዚህ መመሪያ በተባእታይ ፆታ የተገለፀው እንደቃሉ አገባብ ለአንስታይ ፆታም ያገለግላል፡፡

# <u>ክፍል ሁለት</u>

# <u>ተግባር እና ኃላፊነት</u>

## <u>አንቀፅ አምስት</u>

## <u>የስራ ክፍሎች ተግባር እና ኃላፊነት</u>

የስራ ክፍሎች የሚከተሉት ተግባርና ሀላፊነቶች ይኖራቸዋል፦

1. ክስ ወይም ማንኛውም የፍትህ አካላት መጥሪያ ሲመጣ ክሱ ወይም መጥሪያው በደረሰበት እለት ለደጋፊ የስራ ሂደቱ የመላክ፤

2. ክሱን ወይም መጥሪያውን ተከትሎ ደጋፊ የስራ ሂደቱ ማስረጃ ሲጠይቅ አስፈላጊውን ማስረጃ በደብዳቤው በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ የመላክ፤
3. በደጋፊ የስራ ሂደቱ ከተጠየቀው ጉዳይ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሰነዶች ሳያስቀሩ በሙሉ የመላክ፤
4. ክስ እንዲመሰረት ደጋፊ የሰራ ሂደቱ በተጠየቀ ጊዜ በደብደቤ የተጠቀሱትንና ለክሱ የሚያስፈልጉ ዝርዝር ማሰረጃዎች የመላክ፤
5. ደጋፊ የስራ ሂደቱ ማብራሪያ ሲጠይቅ ተገቢው ሙያዊ ማብራሪያ በፅሁፍ አዘጋጅቶ የመላክ፣
6. የሕግ አስተያየት እንዲሰጣቸው ሲጠይቁ አስተያየት የሚጠይቁበትን ፍሬ ነገር በግልጽ ዘርዝሮ የማስቀመጥና ጥያቄውን ተከትሎ ደጋፊ የስራ ሂደቱ የሚጠይቀው ማስረጃ ካለ ይህንኑ የመላክ፣

## አንቀጽ ስድስት

## ባለስልጣኑ ከገባቸው ውሎች ጋር በተያያዘ ክስ መመስረት ሲያስፈልግ ወይም ክስ ሲመሰረትበት ምላሽ ለመስጠት የሚያስፈልጉ መረጃዎችና ማስረጃዎች

1. ውል የተገባው በጨረታ ከተፈጸመ ግዥ ጋር በተያያዘ ከሆነ የጨረታው ሙሉ ሰነድ፤
2. ሙሉ የውል ሰነድ፤/የውል ማሻሻያዎች ካሉ እነሱን ጨምሮ/
3. ክፍያ የተፈጸመባቸው ሰነዶች፤
4. ከተዋዋይ ጋር የተደረገ የስብሰባ ቃለ-ጉባኤዎች፤
5. የተሰጡ ማስጠንቀቂያዎች፤
6. ዉሉ የተቋረጠበት ደብዳቤ ከበቂ ማብራሪያ ጋር፤
7. የተገቡ የመልካም ስራ አፈጻጸም ዋስትናዎች እና
8. ሌሎች ከጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሰነዶች፤

## አንቀጽ ሰባት

## የውሃ እዳ ክስ እንዲመሰረት ለሚቀርቡ ጥያቄዎች የሚያስፈልጉ መረጃዎችና ማስረጃዎች

1. ደንበኛው ውሃ እንዲገባለት የጠየቀበት ማመልከቻ / ደንበኛው ተቋም ከሆነ ውክልና ጨምሮ/፤
2. ውሃ እንዲገባ የተሰጠ የስራ ትዕዛዝ፤

3. ደንበኛው ከመ/ቤቱ ጋር የገባው ውል፤
4. የእዳ ማረጋገጫ ሰነድ በየወሩ ከተተነተነ ውዝፍ እዳ ዝርዝር ጋር፤
5. ቆጣሪው በእዳ ምክንያት የተነሳ ከሆነ እንዲነሳ የተሰጠ የስራ ተዕዛዝ፤
6. የተነሳ ቆጣሪ ገቢ የተደረገበት ደረሰኝ፤
7. ባለዕዳው ካለው ተቀማጭ ሂሳብ ላይ ዕዳው ተቀናንሶ ልዩነቱን የሚያሳይ መግለጫ፣
8. ሌሎች የተካሄዱ መፃፃፎች ወይም ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶ ከሆነ ይሄንኑ፣

## አንቀጽ ስምንት

## በባለስልጣኑ ንብረት ላይ ጉዳት ሲደርስ ከውል ውጪ ክስ እንዲመሰረት ለሚቀርቡ ጥያቄዎች

## የሚያስፈልጉ መረጃዎችና ማስረጃዎች

1. ጉዳቱን ያደረሰው ሰው/ተቋም ሙሉ ስም ከነአድራሻው/ጉዳት ያደረሰው በተሸከርካሪ ከሆነ የአሽከርካሪው ስምና የተሸከርካሪው ሰሌዳ ቁጥር፣ የተሸከርካሪው ሊብሬ፣ የአሽከርካሪው መንጃ ፈቃድና ለትራፊክ የተመዘገበ ከሆነ የጥፋተኝነት ማረጋገጫ ደብዳቤ፣
2. ጉዳቱ የደረሰበት ሰዓት፣ቀን እና ልዩ ቦታው፤
3. ጉዳቱ የተከሰተበት ሁኔታ ወይም የአጋጣሚው ሁኔታ ማብራሪያ፤
4. ጉዳት ስለመድረሱ ከጉዳት አድራሹ ጋር የተፈረመ  መተማመኛ፤
5. ጉዳቱ ስለመድረሱና ጉዳቱ የተከሰተበትን ሁኔታ የሚያስረዱ ሶስት የሰው ምስክሮች፤
6. ጉዳት የደረሰበት ንብረት ግምት ከተገዛበት ደረሰኝ ጋር ይህ ካልተቻለ ግምቱ በባለሙያ ተሰልቶና ይኸው በአማርኛ ተተርጉሞ፣ በባለሙያው ፊርማ ተረጋግጦ ፤ የሃላፊ ቲተር፣ ፊርማ አርፎበት እና ማህተም ተደርጎበት ጊዜ ገደቡን ጠብቆ እንዲቀርብ፣

## አንቀጽ ዘጠኝ

## የወንጀል ክስ እንዲመሰረት ለሚቀርቡ ጥያቄዎች የሚያስፈልጉ መረጃዎችና ማስረጃዎች

1. የወንጀል ድርጊቱን የፈጸመው ተጠርጣሪ ሙሉ ስም ከነአድራሻው፣
2. የወንጀል ድርጊቱ የተፈጸመበት ክ/ከተማ ፣ልዩ ቦታ፣ቀን እና ሰዓት፣
3. የወንጀል ድርጊቱ የተፈጸመበት የንብረት ግምት፣
4. የወንጀል ድርጊቱ ሲፈጸም የነበሩ ወይም የሚያውቁ እማኞች /ምስክሮች/፣

5. ወንጀሉ ፖሊስ ጣቢያ ተመዝግቦ ከሆነ የተመዘገበበት ፖሊስ ጣቢያ እና የመርማሪ ፖሊስ ስም፣

## አንቀጽ አስር

## ባለስልጣኑ ከሰራተኛ አስተዳደር ጋር በተያያዘ ክስ እንዲመሰረት ሲያስፈልግ ወይም ክስ ሲመሰረትበት ምላሽ ለመስጠት የሚያስፈልጉ መረጃዎችና ማስረጃዎች

1. የሰራተኛው የስራ ውል፣
2. እንደአስፈላጊነቱ ሲጠየቅ የሰራተኛው የግል ማህደር፣
3. ሰራተኛው የፈፀመው ድርጊት እና እንዲከሰስ የተፈለገበት ዝርዝር ምክንያት ከነማስረጃዉ፣
4. የገንዘብ/የንብረት ጉድለት ከሆነ ንብረቱን የተረከበበት ሰነድና የተሟላ የኦዲት ሪፖርት፣

## አንቀጽ አስራ አንድ

## ባለስልጣኑ ከኢንሹራንስ ክትትል ጋር በተያያዘ ክስ እንዲመሰረት ሲያስፈልግ ወይም ክስ ለማቅረብና ምላሽ ለመስጠት የሚያስፈልጉ መረጃዎችና ማስረጃዎች

1. የተሽከርካሪውን ጉዳት ግምት፣ የፖሊስ ሪፖርት እና የጉዳት አድራሹ ተሽከርካሪ ባለቤትና አሽከርካሪ አስመልክቶ የተደራጁትን በትራፊክ ፖሊስ የተፃፈ አጥፊውን የሚያመለክት ደብዳቤ ማቅረብ፣
2. የታደሰ የኢንሹራንስ ፖሊሲ ኮፒ አያይዞ የመላክ፣

## አንቀጽ አስራ ሁለት

## ሁከት ይወገድልኝ ክስን በተመለከተ የሚቀርብ ማስረጃ

1. ሁከት የተፈጠረበት ንብረት አይነትና ግምቱ፣
2. ሁከት የተፈጠረበት ቦታ፣ቀን፣ ሰዓትና ዓ.ም፣
3. ሁከት የፈጠረው አካል /ሰው/ ስምና አድራሻ፣
4. ሁከት መፈጠሩን የሚመሰክሩ ቢያንስ ሶስት የሰው ምስክሮች ከነአድራሻቸው ማቅረብ፣
5. ሁከት የተፈጠረበት ንብረት የባለሀብትነት ወይም የባለይዞታነት ማስረጃ፣

## አንቀጽ አስራ ሶስት

## የሕግ አስተያየት ለመስጠት የሚያስፈልጉ መረጃዎችና ማስረጃዎች

የህግ አስተያየት እንዲሰጥበት ለሚቀርብ ጥያቄ ከጉዳዩ ጋር አግባብነት ያላቸው ማስረጃዎች ደጋፊ የስራ ሂደቱ በጠየቀ ጊዜ ማቅረብ ፤

## ክፍል ሶስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## አንቀጽ አስራ አራት

## የመተባባር ግዴታ

1. የሥራ ክፍሎች የክስና መልስ ማስረጃ አላላክና አቀራረብ በዚህ መመሪያ በተመለከተው ድንጋጌ መሰረት በወቅቱና በሰዓቱ መረጃውን የመስጠት ሃላፊነት አለባቸው፡፡
2. ማንኛውም የስራ ክፍል ይህንን መመሪያ ተግባራዊ ለማድረግ በሚደረግ እንቅስቃሴ የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

## አንቀጽ አስራ አምስት

## ተጠያቂነት

1. ተገቢዉን ማስረጃ ለመሰብሰብ ጥረት ያላደረገ ወይም ሳያሰባስብ ክስ የመሰረተ ወይም መልስ የሰጠ የደጋፊ የስራ ሂደቱ የህግ ባለሙያ፣ ማስረጃዉ ባለመቅረቡ በመ/ቤቱ ላይ ለሚደርሰዉ ጉዳት ወይም መ/ቤቱ ለሚያጣዉ ጥቅም ተጠያቂ ይሆናል፤
2. ተገቢዉ ማስረጃ መሰባሰቡን ሳያረጋግጥ ክስ ወይም መልስ ላይ ማረጋገጫ የሰጠ ሃላፊ በጉዳዩ ላይ መ/ቤቱ ለሚያጣዉ ጥቅም እና ለሚደርስበት ጉዳት ተጠያቂ ይሆናል፤
3. ከማንኛውም የፍትህ አካላት ለመ/ቤቱ መጥሪያ ሲላክ መጥሪያው በደረሰበት እለት ለደጋፊ የስራ ሂደቱ በወቅቱ ሳይደርስ ቀርቶ በመ/ቤቱ ላይ ለሚደርሰዉ ጉዳት መጥሪያዉን ያልላከዉ የስራ ክፍል ሃላፊ ወይም ሰራተኛ ተጠያቂ ይሆናል፤
4. ደጋፊ የስራ ሂደቱ ክስ ወይም መልስ ለማዘጋጀት እንዲያስችለዉ ማስረጃ ሲጠይቅ አስፈላጊውን ማስረጃ በደብዳቤው በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ያልላከ ሃላፊ ወይም ሰራተኛ ተጠያቂ ይሆናል፤

5. በፍታብሄር እና በወንጀል ህጉ ላይ ያለዉ ተጠያቂነት እንደተጠበቀ ሆኖ ከላይ ከተ.ቁ 1-4 የተጠቀሰዉ ተጠያቂነት ያለበት ሃላፊ ወይም ሰራተኛ በመ/ቤቱ የሥራ መሪዎች መተዳደሪያ መመሪያ እንዲሁም በህብረት ስምምነቱ መሰረት በተመሳሳይ ጥፋት የሚያስቀጣዉን ቅጣት ይቀጣል፡፡

## አንቀጽ አስራ ስድስት

## መመሪያውን ስለማሻሻል

ይህ መመሪያ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማንኛውም ጊዜ በከፊል ወይም በሙሉ ሊሻሻል ይችላል፡፤

## አንቀጽ አስራ ሰባት

## መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በዋናው ሥራ አስኪያጅ ከተፈረመበትና የመስሪያ ቤቱ ማህተም ካረፈበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን**

**ዋና ሥራ አስኪያጅ**

**አውቀ ኃይለሚ ያም**